# ለመጀመርያው የህይወት ሳምንት

## የወላጅ መመርያ

## አዲስ የወለዱት ህጻን ደህና ነውን?

### ጤናማ አዲስ የተወለደ ህጻን:

- ሐምራዊ ከንፈርና ሐምራዊ ምላስ አለው
- ከእርስዎ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ከ36.8°C እስከ 37.3°C የሚደርስ የብብት ሙቀት መጠን ያለው
- አዘውትሮ ሽንት ይሸናል፣ ሰገራም ይወጣል
- ምግብ ብዙ ጊዜ፣ በ 24 ሰዓቶች ውስጥ ከ 8-12 ጊዜ ይበላል
- ከእንቅልፍ በሚነቃበት ጊዜ በጸጥታ ይነቃል፣ ለሰውና ለሌላ ድምጽ ምላሽ ይሰጣል
- ከአንዳንድ አጫጭር ለአፍታ ትንፋሽ ከሚያቆምባቸው ባሻገር፣ ከእርስዎ ትንሽ ፈጥኖ ይተነፍሳል
- ሲቸገሩና እርዳታ ሲፈልጉ ምልክት ያሳያሉ፣ ለምሳሌ ቀለም መቀየር፣ ማልቀስ፣ መቁነጥነጥ ወይም መንቀጥቀጥ።

## አዲስ የወለዱት ህጻን ታሟልን?

ህጻን ልጅዎ:

- መተንፈስ ካቆመ ወይም ወደ ሰማያዊ ከተቀየረ
- የሚጥል በሽታ ካለበት፣ የዓይን፣ አፍ፣ ክንዶች ወይም እግሮች ድንገት መንቀጥቀጥ ወይ መንቀሳቀስ
- ከእንቅልፍ ሊነቃ ካልቻለ
- ኃይለኛ ድምጾችን፣ በዓይኖቻቸው ውስጥ የሚያበራ ደማቅ ብርሃን ወይም በእጃቸው ላይ ለስለስ ያለ መቆንጠጥ ካላስተዋለ።

### የሚወሰድ እርምጃ

**ሆስፒታል ውስጥ**

**ወዲያውኑ** ለአዋላጅዎ ወይም ለሀኪምዎ ይንገሩ፤ ወይም በስልክ የእርዳታ መደወያን መጫን

**በቤት ውስጥ**

**000 ይደውሉ**

## በህይወት የመጀመሪያ ሳምንት ውስጥ

ህጻን ልጅዎ:

- ከተወለደ በኋላ ባሉት የመጀመርያዎቹ 24 ሰዓታት ቢጫ መልክ ያለው ቆዳ ካለው
- ከመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት በኋላ ከ6 ሰዓታት በላይ ካልተመገበ
- ከመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት በኋላ በቀን ቢያንስ 1 እርጥብ እና 1 ቆሻሻ ጨርቅ/ናፒ ካላደረገ
- ድንገት የሚንቀጠቀጥ ወይ የሚንቀሳቀስ ዓይን፣ አፍ፣ ክንድ ወይም እግር ካለበት
- በሰውነት፣ በጭንቅላት፣ በአንገት፣ በእጆቻቸውና በእግሮቻቸው ላይ የሚልፈሰፈስ ወይም የሚያነክስ ከመሰለ
- በጣም በፍጥነት ይተነፍሳል እና ያልተለመደ ድምጽ ካሰማ
- ያልተለመደ ማልቀስ - ልክ እንደ ደካማ፤ ቀጠን ያለ ድምጽ፤ የሚያቃስት ወይም የሚያሰቃይ ማልቀስ ሲኖሩት
- በሰገራቸው ውስጥ ደም ካለ
- በጣም የገረጣ ቆዳ ወይም ወደ ቢጫ ቀለም የሚሄድ ካላቸው
- በሚተነፍሱበት ግዜ ሆዳቸው ወይም የደረታቸው የታችኛው ክፍል ወደ ውስጥ ከገባ
- ብዙ ካስታወከው- ከእያንዳንዱ የመጨረሻ 3 ምግቦች በኋላ ከግማሽ በላይ የሚሆነው።
- ትውከቱ ቀለም የሌለው፣ ወተታማ ወይም የገረጣ ቢጫ ከሆነ ነው።

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ንጹህ | ወተት | የደበዘዘ ብጫ | ሰናፍጭ | አረንጓዴ | አረንጓዴ | አረንጓዴ | አረንጓዴ | ደም |

ወይም

- የሆነ ችግር እንዳለ ሆኖ ከተሰማዎት

### የሚወሰድ እርምጃ

**ሆስፒታል ውስጥ**

ለአዋላጅዎ ወይም ለሀኪምዎ ይንገሩ።

**ቤት ውስጥ**

- የ24-ሰዓት የወላጅና ህጻን ጤና መስመር ስልክ 13 22 29
- የ24-ሰዓት ተጠባባቂ ነርስ ስልክ 13 60 60 24
- ወደ አካባቢዎ ሀኪም (GP) ይሂዱ
- ወደ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ
- አስቸኳይ ከሆነ **000 ይደውሉ**

**እባክዎን ያስተውሉ፡ በስክሪን ላይ ሲታዩ እና/ወይም ሲወርዱ (ዳውንሎድ ሲደረጉ) እና ሲታተሙ፣ በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉት ቀለሞች እንደ መሳሪያዎ ቅንብሮች ሊለያዩ ይችላሉ።**

Reference: Morley CJ, Thornton AJ, Cole TJ, Hewson PH, Fowler MA. Baby Check: a scoring system to grade the severity of acute systemic illness in babies under 6 months old. Arch Dis Child. 1991 Jan;66(1):100-5. doi: 10.1136/adc.66.1.100.